


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ. ሞንሰን

# ስራውን ማፍጠን

በዳግም የተመለሰችው ቤተክርስቲያን 100 ካስማዎች ከመኖሯት በፊት 98 አመቷ እንደነበር ታውቃላችሁ? ነገር ግን ከ30 አመት በኋላ፣ ቤተክርስቲያኗ ሁለተኛውን 100 ካስማዎች አደራጀች። እናም ከዚያ ከስምንት አመት በኋላ ቤተክርስቲያኗ ከ300 በላይ ካስማዎች ነበሯት። ዛሬ ከ3 ሺህ በላይ የሆኑ ካስማዎች አሉን።

ይህ እድገት ለምን በፍጥነት እየሄደ ነው? እኛ በደንብ እየታወቅን ስለሆነ ነውን? አስደሳች የማምለኪያ ህንፃዎች ስላለን ነውን?

እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ናቸው፣ ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ዛሬ የምታድግበት ምክንያት ጌታ እንደሚሆን ስላመለከተ ነው። በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ፣ እንዲህ አለ፣ "እ ነሆ፣ ስራዬን በራሱ ጊዜ እንዲፈጥን አደርጋለሁ"[1]

እኛ፣ እንደ ሰማይ አባታችን መንፈስ ልጆች፣ በዚህ ጊዜ ወደ ምድር የተላክነው ይህን ታላቅ ስራ ለማፍጠን እንድንሳተፍ ነው።

ባለኝ እውቀት ውስጥ፣ ጌታ ስራው በስጋዊ ህይወት ብቻ እንደሚወሰን አመልክቶም አያውቅም። ግን፣ ስራው ዘለአለምን የሚያቅፍ ነው። ስራውን በመንፈስ አለም እያፈጠነ እንደሆነ እምነት አለኝ። ጌታ በዚያ በሚገኙ አገልጋዮቹ በኩል መንፈሶች ወንጌል እንዲቀበሉ እያዘጋጀ እንደሆነም አምናለሁ። ስራችንም ሙታኖቻችንን እንድንፈልግ እናም ወደ ቤተመቅደስ እንድንሄድና ከመጋረጃው አልፈው የሄዱትን እኛ ያለንን አይነት እድል የሚያመጣላቸውን ቅዱስ ስርዓቶች እንድናከናውን ነው።

ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ (1801–1877) እንዳሉት፣ በመንፈስ አለም ያሉ መልካም የኋለኛው ቀን ቅዱሳንም በስራ ተጠምደዋል። "በዚያ ምን እያደረጉ ነው? እነርሱም እየሰበኩ፣ በሁሉም ሰዓት እየሰበኩ፣ እናም እዚህ እና በሌሎች ቦታዎችም ቤተመቅደስ የምንገነባበትን ስራዎቻችን የምናፈጥንበትን መንገዶችን እያዘጋጁ ናቸው።"[2]

አሁን፣ የቤተሰብ ታሪክ ስራ ቀላል አይደለም። ለእናንተ ከስካንዴኔቪያ ለመጣችሁት፣ ብስጭታችሁን እጋራለው። ለምሳሌ፣ ከስዊድን ከመጡት ዘሮቼ፣ የአያቴ ስም ኔልስ ሞንሰን ነበር፤ የእርሱ አባት ስም ሞንሰን ሳይሆን ሞንስ ኦክሰን ነበር። የሞንስ አባት ስም ኦክ ፔደርሰን ነበር፣ እናም የእርሱ አባት ስምም ፒተር ሞንሰን ነበር—እንደገናው ወደ ሞንሰን ይመለሳል።

ጌታ እኔ እና እናንተ የቤተሰብ ታሪካችንን በደንብ እንድናከናውን ይጠብቃል። ስራችንን በደንብ ለማከናወን መጀመሪያ ማድረግ የሚያስፈልገን የሰማይ አባታችን መንፈስ ከእኛ ጋር እንዲሆን ማድረግ እንደሆነ ይሰማኛል። በጽድቅ ለመኖር እንደምናውቀው ስንኖር፣ በቅንነት እና በትጋት የምንፈልጋቸውን በረከቶች ለማሟላት መንገዶች ይከፍትልናል።

ስህተቶች እንሰራለን፣ ነገር ግን ማንኛችንም በመጀመሪያ ጀማሪ ሳን ሆን በቤተሰብ ታሪክ ስራ ባለሙያ ለመሆን አንችልም። ስለዚህ፣ ወደዚህ ስራ በመዝለል መጀመር አለብን፣ እናም ከባድ ነገሮችን ለማከናወንም መዘጋጀት ይገባናል። ይህም ቀላል ስራ አይደለም፣ ነገር ግን ጌታ ይህን በእናንተ ላይ አሳርፏል፣ እናም በእኔም ላይ ይህን አሳርፏል።

የቤተሰብ ታሪክ ስራን ስታከናውኑ፣ የሚያሰናክል ያጋጥማችኋል፣ እናም ለእራሳችሁም "ሌላ ማድረግ የምችለው ነገር የለም" ትላላችሁ። እዛ ቦታ ላይ ስትደርሱም፣ ተንበርከኩ እናም ጌታ መንገድን እንዲከፍትላችሁ ጠይቁ፣ እናም መንገድን ይከፍትላችኋል። ይህም እውነት እንደሆነ እመሰክራለሁ።

የሰማይ አባት ልክ እኔንና እናንተን እንደሚወደን ያህል በመንፈስ አለም ያሉትን ልጆቹን ይወዳል። የሞቱብንን የማዳን ስራ በተመለከተ፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንዳሉት፣ "እናም አሁን የእግዚአብሔር ታላቅ

አላማዎች ወደ ሚከናወኑበት ደረጃ ሲፈጥኑ፣ እና ነቢያት የተናገሩት ሲሟሉ፣ የእግዚአብሔር መንግስት በምድር ላይ ስትመሰረት፣ እና የጥንት ነገሮች ስርዓት በዳግም ሲመለሱ፣ ጌታ ይህን መጋቢነት እና እድል ለእኛ ገልጿል።”[3]

ስለወንጌሉ ሳያውቁ ስለሞቱት ቅድመ አያቶቻችን በሚመለከትም፣ ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ. ስሚዝ (1838–1918) እንዳወጁት፣ “ለእነርሱ በምናደርገው ጥረት በኩል የታሰሩበት ሰንሰለቶች ይወድቃሉ፣ እናም ብርሀን እንዲበራባቸው እና በመንፈስ አለም በልጆቻቸው ለእነርሱ የተከናወነውን ስራ እንዲሰሙ፣ የከበባቸው ጭለማም ይበተናል፣ እናም ከእናንተ ጋር ሀላፊነቶቻችሁን ባከናወናችሁት ይደሰታሉ።”[4]

ከመሞታቸው እና ወደ መንፈስ አለም ከመሄዳቸው በፊት የክርስቶን ስም ሰምተው የማያውቁ በብዙ ሚልዮን ቁጥር የሆኑ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጆች አሉ። ነገር ግን ወንጌሉን ተምረዋል እናም ወደ ጌታ ቤት ለመሄድ እና እነርሱ ለማከናወን የማይችሉትን ስራ ለእነርሱ ለማከናወን እንድንችል የሚያደርግ መንገድን ለማጽዳት የሚያስፈልገውን ጥናት እናንተ እና እኔ የምናደርግበትን ቀን እየጠበቁ ናቸው።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ስራውን ስንቀበል እና መልስ ስንሰጥ ጌታ እንደሚባርከን እመሰክራለሁ።

---

### ከዚህ መልእክት ማስተማር

ከቤተሰባችሁ ታሪክ ውስጥ የምትወዱትን ታሪክ አስቡ እና ይህን ታሪክ ከምትጎበኟቸው ጋር አካፍሉ። የምትጎበኟቸው ን ሰዎች ታሪኮቻቸውን እንዲካፈሉ ለማበረታታት በቀዳሚ አመራር መልእክት በልጆች ክፍል (ገጽ 6) ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ለመጠቀም ትፈልጉ ይሆናል። ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 128፥15ን ለማንበብ እና የቤተመቅደስ ስርዓቶችን በቅድመ አያቶቻችን ስም የማከናወን አስፈላጊነት ላይ ለመወያየት አስቡበት።

ማስታወሻዎች

1. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 88፥73።
2. *Teachings of Presidents of the Church: Brigham Young,* [1997 (እ.አ.አ)]፣ 208።
3. *Teachings of Presidents of the Church: Joseph Smith,* [2007 (እ.አ.አ)]፣ 409።
4. *የቤተክርስትያኗ ፕሬዘደንቶች ትምህርቶች፣ ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ,* 1998 (እ.አ.አ)፣ 247።

## ወጣቶች

# የቅድመ አያቶችን ስም በፊደል በተራ መዘርዘርን ልወደው እችላለሁን?

**በኤማ አብሪል ቶሊዶ ሲስኔሮስ**

50 ሺህ የቅድመ አያት ስሞችን በፊደል በተራ ለመዘርዘር ካስማችን በነበራት አላማ ተሳትፌ ነበር። በመጀመሪያ አስቸጋሪ ነበር። በተለያዩ ጊዜዎች ከኮምፒውተር ያገኘኋቸው መዝገቦች ለማንበብ በሚያስቸግር የእጅ ጽሁፍ የተጻፉ ነበሩ፣ እናም አንዳንዴም ለመመለስ እና ሌላ መዝገብ ከኮምፒውተር ለማግኘት እፈልግ ነበር። ነገር ግን ሁሉም ሰዎች እንደዚህ የሚያስቡ ከሆኑ፣ እነዚህ መዝገቦች በመጨረሻ ለመፈጸም እንደሚቀሩ ገባኝ። በመንፈስ አለም የተሰለፉ ብዙ ሰዎች በአዕምሮዩ ማየት እችል ነበር፣ እናም እነዚህን ስሞች ለማንበብ እና ያለስህተት ለመጻፍ በመሞከር ለመቀጠል ወሰንኩኝ።

ለእነዚያ ሰዎች ፍቅር እንዲኖረኝ ተማርኩኝ። እነርሱ በእውነትም እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው፣ እና እኛም ከእነርሱ እርዳታ እደሚያስፈልገን ተረዳሁ። የሰማይ አባት ፍጹም አላማ በሁሉም ሰዎች ላይ እንደሚያስብበት በደንብ ለመረዳት ቻልኩኝ። በእርሱ የተመረጡ መሪዎችን መመሪያዎች እና ትምህርቶች ስንከተል፣ ስለእርሱ ምህረት እና መጨረሻ ስለሌለው ፍቅር ምስክር ለመሆን እንችላልን።

የቅድመ አያቶችን ስም በፊደል በተራ መዘርዘር ለእኔ የሚያስደስት አጋጣሚ ነበር። ስለቤተሰብ ታሪክ ብዙ ነገሮችን እንዳፈቅር እና ታላቅ ዋጋ እንድሰጥ ተማርኩኝ። የቅድመ አያቶችን ስም በፊደል በተራ በመዘርዘር ላይ በመሳተፍ ታዛዥ በመሆንም ከጌታችን ታላቅ ዋጋ ያላቸው ን ስጦታዎች አገኘሁ።

*ደራሲዋ በቬራክሩዝ፣ ሜክሲኮ ትኖራለች*

## ልጆች

# ታሪካችሁን እወቁ

ወላጆቻችሁ እና አያቶቻችሁ ብዙ ጀብዶች ነበሯቸው—አንዳንዶቹን እናንተም አታውቋቸውም! ከታሪኮቻቸው አንዳንዶቹ፣ ያስቋችኋል፣ እናም በሰማይ አባት እምነት እንዲኖሯችሁ ሊረዷችሁም ይችላሉ። ነገር ግን አንዳንዴ ጎልማሶችም ሊያፍሩ ይችላሉ። የሚወዷቸውን ታሪኮች እንዲያስታውሱ ለመርዳት እነዚህን ጥያቄዎች ተጠቀሙ እናም መልሳቸውን ጻፉ ወይም በስ እል ሳሉ።

1. ከትዝታዎቻችሁ የሚያስደስቷችሁን ሶስቱን ንገሩኝ።
2. ከሁሉም በላይ የሚያሳፍራችሁ የነበረ ሁኔታ ምን ነበር?
3. ስለተወለድኩበት ቀን ንገሩኝ?
4. በልጅነታችሁ ምን ማድረግ ትወዱ ነበር?
5. ስለወንጌል ምስክርነታችሁን እንዴት አገኛችሁ?

© 2014 by Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, June 2014.* Amharic. 10866 506 ትርጉም

# የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ተልዕኮ፥ ምሳሌ

*በጸሎት መንፈስ ይህንን መረጃ አንብቡት እና ምን እንደምታካፍሉ ለማወቅ ጣሩ። የአዳኝንን ህይወት እና ተልእኮ መረዳት በእርሱ ያላችሁን እምነት የሚያሳድገው እና በሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት ምክንያት የምትንከባከቧቸውን የሚባርከው እንዴት ነው? ለተጨማሪ መረጃ ወደ ሂዱ reliefsociety.lds.org።*

እምነት • ቤተሰብ • እርዳታ

*ይህ የአዳኝን ተልዕኮ ሁኔታዎችን የሚያስመለክቱ የተከታታይ የሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት መልእክቶች ክፍል ነው።*

ሌሎችን ስናገለግል፣ ለእኛ ምሳሌ ለነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች እንሆናለን። ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ. ሞንሰን እንዳሉት፥ "እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ተከበናል። በዚህ ምድር ላይ እኛ ልጆቹን የማገልገል እና የማንሳት ጭምር አደራ ያለን የጌታ እጆች ነን።"[1]

የሴቶች መረዳጃ ማህበር አጠቃላይ ፕሬዘደንት ሊንዳ ኬ. በርተን እንዳስተማሩት፥ "በልምምድ፣ የእግዚአብሔርን ልጆች ስናገለግል እያንዳንዳችን እንደ አዳኝ ለመሆን እንችላለን። እርስ በራስ [ለማገልገል] እንድንችል እንዲረዳን፣ የምናስታውሳቸው አራት ቃላቶችን በሀሳብ አቀርባለው፥ 'መጀመሪያ ተመልከቱ፣ ከዚያም አገልግሉ።' . . . ይህን ስናደርግ፣ ቃል ኪዳኖችን እንጠብቃለን፣ እናም ፕሬዘደንት ሞንሰን እንዳሉትም፣ አገልግሎታችንም የደቀመዛሙርትነታችን ምልክት ይሆናል።[2]

በየጠዋት ሌሎችን ለማገልገል ያሉንን እድሎች ለማወቅ መጸለይ እንችላለን። የወጣት ወንዶች አጠቃላይ ፕሬዘደንት ዴቪድ ኤል. ቤክ እንዳሉት "የሰማይ አባት ይመራችኋል፣ እናም መላእክቶችም ይረዷችኋል።" "ህይወቶችን ለመባረክ እና ነፍሶችን ለማዳን ሀይል ይሰጣችኋል።"[3]

## *ከቅዱሳት መጻህፍት*

ማቴዎስ 20፥25–28፤ 1 ኔፊ 11፥27–28፤ 3 ኔፊ 28፥18

## *ከታሪካችን*

በጥቅምት 1856 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ፣ ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ (1801–77) የእጅ ጋሪ የሚገፉ ፈር ቀዳጆች ሜዳዎችን እየተሻገሩ እንዳሉ እና ሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ወዲያው በመሰብሰብ እንዲረዱ አወጁ። ሴቶች "ሽርጦቻቸውን ፣ የእግር ሹራቦቻቸውን፣ እና በትርፍ ያላቸውን ነገሮች በሙሉ በዚያው በታበርናክል ውስጥ አወለቁ፣ እናም በጋሪዎች ውስጥ ኮለሷቸው" ብለው ሉሲ ሜሰርቭ ስሚዝ ጻፉ።

እንዲድኑ የተደረጉት ፈር ቀዳጆች ወደ ሶልት ሌክ ስቲ ሲደርሱ፣ ሉሲ እንደጻፉት "በህይወቴ በሙሉ ከሰራኋቸው ስራዎች ሁሉ ከዚህ በላይ የሆነ የሚያስደስት አልነበረም፣ እንደዚህ የሚስማማ ስሜት ያሸንፍ ነበር። ወደ ሱቅ ገብቼ የምፈልገውን ማሳወቅ ብቻ ነበር የሚያስፈልገኝ፤ ልብስ ከሆነ፣ ያለ ክፍያ የርዝመትና የስፋት መጠን ይለካ ነበር።"[4]

ፕሬዘደንት ጆርጅ አልበርት ስሚዝ (1870–1951) ሌሎችን ስለማገልገል እንዲህ ብለዋል፥ "የዘለአለም ደስታችን ሌሎችን ለመርዳት እራሳችንን በመስዋዕት በምናሳልፍበት መንገድ የሚመዘን ይሆናል።"[5]

## *ይህን አስቡበት*

**1.** ጸሎት እንዴት በጌታ እጆች መሳሪያዎች እንድንሆን ይረዳናል?

**2.** ሌሎችን ማገልገል ቃል ኪዳኖቻችንን ለመጠበቅ እንዴት ይረዳናል?

ማስታወሻዎች

1. ቶማስ ኤስ. ሞንሰን፣ "What Have I Done for Someone Today?" *Liahona*፣ ህዳር 2009፣ 86።
2. ሊንዳ ኬ. በርተን፣ "*መጀመሪያ ተመልከቱ፣ ከዚያም አገልግሉ፣*" *Liahona*, ህዳር 2012፣ 78፣ 80።
3. ዴቪድ ኤል. ቤክ፣ "*ለማገልገል ያላችሁ ቅዱስ ሀለፊነት፣*" *Liahona*, ግንቦት 2013፣ 56።
4. ጆሴፍ ስሚዝ፣ በ *Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society* ውስጥ (2011)፣ 37።
5. ጆርጅ አልበርት ስሚዝ፣ በ*Daughters in My Kingdom* ሴት ልጆች በመንግስት ውስት፣ 77።

© 2014 by Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) *Visiting Teaching Message, June 2014.* Amharic. 10866 506 ትርጉም